የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አምስተኛ ዓመት ቁጥር ፷፩
አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፩

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

5th Year No. 61
ADDIS ABABA - 29th June, 1999

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፻፸፯/፲፱፻፺፩ ዓ.ም.
የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ቁጥጥር
አዋጅ ...................................................... ገጽ ፩ሺ፻፲፯

## CONTENTS

Proclamation No. 177/1999
Registration and Control of Construction Machinery
Proclamation ........................................ Page 1117

## አዋጅ ቁጥር ፻፸፯/፲፱፻፺፩
## ስለኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ቁጥጥር የወጣ አዋጅ

የኮንስትራክሽን ሥራ ዘርፉን ለማጠናከር የሚያስችል ሁኔታዎችን ማመቻቸት በማስፈለጉ ፤

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል ።

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር ፻፸፯/፲፱፻፺፩" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል ።

፪· ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ ፤

፩· "ሚኒስቴር" ማለት የሥራና ከተማ ልማት ሚኒስቴር ነው ፤

፪· "የኮንስትራክሽን መሣሪያ" ማለት ሚኒስቴሩ በመመሪያ የሚወስነው ለኮንስትራክሽን ሥራ እንዲያገለግል ሆኖ የተሠራ መሣሪያ ሲሆን በክልል ወይም ለፌዴራል መንግሥት ተጠሪ በሆኑ ከተሞች ትራንስፖርትና መገናኛ ቢሮዎች በአዋጅ ቁጥር ፲፬/፹፬ የሚመዘገቡ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን አይጨምርም ፤

፫· "የባለቤትነት መታወቂያ ደብተር" ማለት ለኮንስትራክሽን መሣሪያ ባለንብረቶች የሚሰጥ የባለቤትነት ማረጋገጫ ማስረጃ ነው ፤

፬· "መለያ ቁጥር" ማለት በኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ላይ የሚለጠፍ ፊደል ወይም ቁጥር ወይም ሁለቱም ነው።

## PROCLAMATION No. 177/1999
## A PROCLAMATION FOR THE REGISTRATION AND CONTROL OF CONSTRUCTION MACHINERY

WHEREAS, it has become necessary to facilitate conditions enabling to strengthen the construction sector;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

1. *Short Title*

   This Proclamation may be cited as the "Registration and Control of Construction Machinery Proclamation No. 177/1999."

2. *Definition*

   In this proclamation:

   1) "Ministry" means the Ministry of Works and Urban Development;
   2) "Construction Machinery" means any machinery built for construction purposes and designated as such by the directive to be issued by the Ministry but does not include construction machinery which will be registered, pursuant to Proclamation No. 14/84, by the Transport and Communication Bureaux of Regional States or Cities accountable to the Federal Government;
   3) "Ownership Certificate" means a certificate issued to the owners of a construction machinery.
   4) "Identification Mark" means a letter or number or both affixed to the construction machinery.

፫. ዓላማ

የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ምዝገባና ቁጥጥር ዓላማዎች የሚከተሉት ይሆናሉ ፡

፩. በመንግሥትና በግል ባለቤትነት የተያዙ የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን በዓይነትና በመጠን መዝግቦ ለመያዝ ፡

፪. የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ለዋስትና መያዣና ለመሳሰሉት አገልግሎቶች የሚውሉበትን ሁኔታዎች ለማመቻቸት ።

፬. የሚኒስቴሩ ሥልጣንና ተግባር

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባሮች ይኖሩታል ፤

፩. ለሥራው የሚያስፈልገውን የሰው ኃይልና መሣሪያዎች ያደራጃል ፤

፪. የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን ይመዘግባል፣ የባለቤትነት ደብተር ይሰጣል፣ ወደሀገር ውስጥ ሲገቡም ሆነ ሲወጡ ይቆጣጠራል ፤

፫. ለኮንስትራክሽን መሣሪያዎች መለያ ቁጥር ይሰጣል፣ በመሣሪያዎቹ ላይ መለጠፉንም ይቆጣጠራል ፤

፬. የኮንስትራክሽን መሣሪያዎች ለምርመራ የሚቀርቡበትን ቦታና ጊዜ ይወስናል ፤

፭. የኮንስትራክሽን መሣሪያዎችን ብቃት በመመርመር ማስረጃ ይሰጣል፣ ብቃት የሌላቸውን መሣሪያዎች ሥራ ላይ እንዳይውሉ ይቆጣጠራል ፤

፮. በዚህ አዋጅ በሚወጣ ደንብ በሚወሰነው መሠረት ለሚሰጠው አገልግሎት ዋጋ ያስከፍላል ።

፭. ደንብ ወይም መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩. የሚኒስትሮች ምክር ቤት ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሚረዳ ደንብ ማውጣት ይችላል ።

፪. ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅና በዚህ አዋጅ መሠረት የሚወጣውን ደንብ ለማስፈጸም የሚረዳ መመሪያ ማውጣት ይችላል ።

፮. ቅጣት

ይህን አዋጅ የተላለፈ ማንኛውም ሰው ወይም ድርጅት አግባብ ባለው የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ መሠረት ይቀጣል ።

፯. የተሻሩ ሕጎች

የኢትዮጵያ መንገዶች ባለሥልጣንን እንደገና ማቋቋሚያ (ማሻሻያ) አዋጅ ቁጥር ፩፻፳፪/፲፱፻፹፯ በዚህ አዋጅ ተሽሯል ።

፰. አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከሰኔ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ሰኔ ፳፪ ቀን ፲፱፻፺፩ ዓ.ም

ዶ/ር ነጋሶ ጊዳዳ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዚዳ ት

3. *Objectives*

The objectives of the registration and control of construction machinery shall be the following:

1) register the type and quantity of both government and privately owned construction machineries.
2) facilitate conditions so that construction machineries can be used for mortgage and other similar purposes.

4. *Power and Duties of the Ministry*

The Ministry shall have the following powers and duties:

1) organize personnel and equipment needed for the work;
2) register construction machineries, issue ownership certificate, and supervise the manner they are brought in and out of the country;
3) issue identification marks for construction machineries and ensure that the marks are affixed to the machineries;
4) determine the place and time for the inspection of construction machineries;
5) inspect construction machineries and issue fitness certificate; and ensure that unfit construction machineries are not used for construction purposes;
6) collect fees determined by the Regulations which will be issued in accordance with this Proclamation for the services it renders.

5. *Power to Issue Regulations or Directives*

1) The Council of Ministers may issue Regulations for the implementation of this Proclamation.
2) The ministry may issue a directive for the proper implementation of this Proclamation and the Regulations which will be issued in accordance with this Proclamation.

6. *Penalties*

Any person or organization that contravenes the provisions of this Proclamation shall be punishable in accordance with the relevant penal law.

7. *Repeal*

The Ethiopian Roads Authority Re-establishment (Amendment) proclamation No.122/1995 is hereby repealed.

8. *Effective Date*

This Proclamation shall enter into force as of the 29th day of June, 1999.

NEGASO GIDADA (DR.)

PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ

BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE